DISTRICT OF COLUMBIA
PUBLIC SCHOOLS
Office of the Chief Operating Officer

መስከረም (September) 12, 2016

ውድ ወላጅ ወይንም አሳዳጊ፤

እንደ ትምህርት ባለሙያነታችን፣ የልጅዎ የድኅንነት ዋስትና ለእኛ ከሁሉ ነገር በላይ ቅድሚያችን ነው። ስለዚህም ነው በትምህርት ቤቶ ቻችን ስለ እርሳስ ወይንም ለህማ ምረዛ ብከላ (lead) የውኃ ማጣሪያ ምርመራ፣ ወቅቱን የጠበቀ ውጤት ለማቅረብ የምንጽፍልዎ።

እንደሚያስታውሱት፣ የሕዝብ ጠቅላላ አገልግሎት መምሪያ (DGS) በ 2015-2016 የትምህርት ዓመት ማብቂያ ላይ፣ በዲሲ የሕዝብ ትም ህርት ቤቶች ሕንጻዎች ሁሉ የውኃ ደህንነት ምርመራ አካሂዷል። በዚህም አገልግሎት፣ ምንጮች ሁሉ ተመርምረው የነበሩ ሲሆን፣ የተማ ሪዎች ወላጆችም ስለ ምርመራው ውጤት እንዲያውቁ ይደረጋል። በአጠቃላይ አብዛኛዎቹ በርካታ የምርመራው ውጤቶች ከብከላ ነጻ ሆነው ተገኝተዋል። አንድ የውኃ ምንጭ ከፍ ያለ የእርሳስ ወይንም የለህማ (lead) መጠን ይዞ የሚገኝ ከሆነ፣ ይህ የውኃ ምንጭ አገልግሎት እንዳይሰጥ ይደረግ እና የሕዝብ ጠቅላላ አገልግሎቶች መምሪያ (DGS)፣ የውኃ ማጣሪያ ፊልተር ከማስገባት አንሥቶ፤ ውኃ ከሚሰጠው መሣሪያ እስከ መቀየር ድረስ የሚደረግ ጥረት በማድረግ ችግሩን ይፈታል። ከዚህ በኋላም የወኃው ምንጭ ለመጠጥ ተግባር እንደገና አገልግሎት ላይ እንዲውል የሚደረገው የክትትል ምርመራ ከተደረገለት በኋላ እና የገባለት የማጣሪያ ፊልቴር ስኬታማ መሆኑ ከታየ በኋላ ነው። የዚህም የክትትል ምርመራ፣ ውጤቱን ወላጆች እንዲያውቁት ይደረጋል። የልጅዎን ትምህርት ቤት የውሀ ጥራት ደህንነት ምርመራ ውጤት በዚህ http://dgs.dc.gov/page/water-sampling-results-dc-public-schools. ድረ ገጽ ላይ ያገኙታል።

ለ 2016-2017 የትምህርት ዓመት፣ በጤና መስጫ ክፍሎች፣ ምግብ በሚዘጋጅባቸው ማዕድ ቤቶች የሚገኙ የውኃ ባንቧዎች ምንጮች ሁሉ ጭምር፣ **በሁሉም የመጠጥ ውኃ ምንጮች የውኃ ማጣሪያ ፊልተር ተደርጎላቸዋል።** ከውኃ መጠጫ ፋውንቴኖች (fountains) ጋር የተያያዙ የውኃ ቧንቧዎች ውኃ መስጫው መሣሪያ ጎን ማጣሪያ ፊልተሮች ለመግጠም በዝግጅት ላይ ነን። ከፋውንቴኖች (fountains) ጎን ቀደም ብሎ ማጣሪያ ፊልተር ተገጥሞላቸዋል።

በትምህርት ቤቶች የሚገኙ የውኃ ምንጮች ሁሉ ለመጠጥ ተብለው የተመደቡ አይደሉም። በየመጸዳጃ ቤቱ ወይንም በመማሪያ ክፍሎች የሚገኙ የውኃ ባንቧዎች፣ ለእጅ መታጠቢያነት ንጹሕ ሲሆኑ፣ ነገር ግን ለመጠጥ ውኃነት አገልግሎት ተግባር መዋል ያለባቸው አይደሉም። **ለመጠጥ የማይውሉ የውኃ ምንጮች፣ ተማሪዎች ከእነዚህ ውኃ እንዳይጠጡ ምልክት ተደርጎባቸዋል።**

በ ሀምሌ (July)፣ የዲስ ከተማ መማክርት ጉባዔ በትምህርት ቤቶች እና ሕጻናትን በሚያገለግሉ ድርጅቶች፣ በየስንት ጊዜው የውኃ ምር መራ ድግግሞሽ እንደሚካሄድ እና የሚመረመረው የውኃ መጠን ብዛት ላይ ጫና የሚያስከትል ሕግ (legislation) ያስተዋወቀ ሲሆን ይህም ሕግ በአሁን ሰዓት በመማክርቱ ጉባዔ በመጣራት ላይ ይገኛል። እስከዚያው ግን፣ የሕዝብ ጠቅላላ አገልግሎቶች መምሪያ (DGS) ለዚህ ለተያዘው የትምህርት ዓመት፣ የውኃ ምርመራ ለማድረግ በእቅድ ላይ ነው። የምርመራው እቅድም ተጠናቆ እንዳለቅ ስለዚሁ እቅድ ጉዳይ ወላጆች እንዲያውቁት እናደርጋለን።

በትምህርት ቤት፣ ስለ ብሄራዊ የውኃ ጥራት ደኅንነት ጉዳይ የበለጠ ለመረዳት የከባቢ ጥበቃ ወኪል ድርጅት (EPA) ድረ ገጽ በሆነው በ https: //www.epa.gov/dwreginfo/lead-drinking-water-schools-and-child-care-facilities. ላይ መረዳት ይችላሉ። በተጨማሪም፣ የዋሽንግተ የውኃ እና የፍሳሽ አገልግሎት ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት (WASA) ለዲስትሪክቱ ነዋሪዎች በርካታ አገልግሎቶ ችን የሚያበረክት ሲሆን፣ ድረ ገጹም https://www.dcwater.com/lead/LetterToCustomers.cfm. ነው።

የልጅዎ ጤንነት እና ደህንነት ጉዳይ ለእርስዎ ከማናቸውም ነገር በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው እንደሆነ ሁሉ፣ ለእኛም ከሁሉም በላይ ከፍተኛ ግምት የምንሰጠው ነው። ስለ ልጅዎ ጤንነት የሚያሳስብዎ ጉዳይ ካለ፣ የልጅዎን ሀኪም (pediatrician) እንዲያነጋግሩ ሀሳብ እናቀርባለን። ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን (202) 442-5559 ይደውሉ ወይንም ለ SchoolLeadQuestions@dc.gov. ኢሜይል ያድርጉ። ስለማያሰልሰው ድጋፍዎ እናመሰግንዎታለን።

Carla Watson
ዋና የበላይ ጠቅላይ ሥራ አስኪጅ (Chief Operating Officer)